# መጽሐፈ አስቴር

## ጥናት አንድ አስቴር 1፡1-22

የጥናት ዓላማ፡- አይሁድን ለማዳን ድራማ በሚመስል መንገድ ሁኔታዎቹን ያቀነባበረ እግዚአብሄር፤ ዛሬም ቢሆን የሚወደውንና እንደ ዓይኑ ብሌን የሆነውን ሕዝቡን ለማዳን በሰው ዐይንና አስተሳሰብ በጭራሽ የማይመስሉ ሁኔታዎችን በማቀነባበር ማዳን እንደሚቻለው ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እግዚአብሔር ሕዝቡን አይጥልምና፥ ርስቱንም አይተውምና" መዝ 94፥14

1. አስቴር 1፡1-22 በአንድነት ይነበብ። መጽሐፈ አስቴር ምዕራፍ አንድን በአጠቃላይ በምናነብበት ጊዜ ማየት የምንችላቸው ስንት ግብዣዎች ናቸው? እነዚህ ግብዣዎች በምዕራፉ ውስጥ እያንዳንዱ ግብዣየሚገኙበትን ትክክለኛ ቁጥር ተናገር።
2. ቁ4-8ትን ስንመለከት ክፍሉ የግብዣውን ትልቅነት ከሚናገረው ባሻገር ይህንን ለመረዳት የሚያስችለን ሌላ የምታየው ነገር ካለ ለወገኖች ለመግለጽ ሞክር። በእነዚሁ ቁጥሮች ላይ በመመርኮዝ ንጉሱ ጠረክሲስ ይህንን ያህል ትልቅ፣ ብዙ ወጭና ከፍተኛ ዝግጅት የሚጠይቅ ዓይነት ግብዣን ለማድረግ የተነሳሳበት ዋነኛ ምክንያቱ ምን ነበረ?
3. በቁ10-15 ላይ ስናነብ ንጉሱ ይህንን ትልቅና ህዝብን ሁሉ ማስገረም የሚችል ግብዣ ካካሄደ በኋላ ሕዝቡን፣ እንዲሁም ሹማምንቱንና መኳንንቱን በይበልጥ ለማስገረም ለመውሰድ የወሰነው እርምጃ ምን ነበረ? በእነዚሁ ቁጥሮች ላይ ስንመለከት ይህ በስተ መጨረሻው ሊያደርገው የወሰነው የማስገረሚያ ትዕይንት እንደሌላው ነገር በቀላሉ ሊሳካለት ያልቻለበት ምክንያት ለምን ነበረ?
4. "አገልጋዮቹ የንጉሡን ትእዛዝ በነገሯት ጊዜ ግን፣ ንግሥት አስጢን መሄድ አልፈለገችም" መጽሐፍ ቅዱሳችን ንግሥት አስጢን ወደ ንጉሱ ለመሄድ እንቢ ማለቷን እንጂ ለምን እንቢ እንዳለች አይነግረንም። ቁ10 ላይ ንጉሱ ንግሥቲቱን እንድትመጣ ለማድረግ ያነሳሰው ነገር ምን እንደነበረ ስናይና በሌላ በኩል ደግሞ ንግሥት አስጢንም የራሷ የሆነ ግብዣ ላይ እንደነበረች ስንመለከት ለአስጢን እንቢታ አስተዋጽዖ ሊኖረው ይችላል የምትለው ምን ነገር ይታይሃል? መጠጥ በሰዎች ውሳኔ ላይ ሊያስከትል ስለሚችለው ያልተጠበቀ መጥፎ ውጤት ምን ምን መማር እንችላለን?
5. በቁ15-22 ላይ ንጉሱ በተለይም በቁ15 ላይ ሊቃውንቱን "በጃንደረቦቹ በኩል የተላከባትን የንጉሥ ጠረክሲስን ትእዛዝ ስላልፈጸመች፣ በሕጉ መሠረት በንግሥት አስጢን ላይ ምን መደረግ አለበት?" ለሚለው ጥያቄው የሰጡትን ምላሽ በጣም አጠር ባለ መልኩ ተናገር።
6. የግብዣው መጠራት፣ የንጉሱ ንግሥቲቱን መጥራት፣ የንግሥቲቱ ለመሄድ እንቢ ማለት፣ የአማካሪዎቹ ምክርና የመሳሰሉትን ሁሉ ነገሮች መቀነባበር ስታይ ሁኔታዎቹን ከአስቴር ወደ ንግሥትነት ከመምጣት ጋራ እንዴት ትመለከታቸዋለህ? ባላወቅኸውና ባልተረዳኸው መንገድ እግዚአብሄር ነገሮችን አቀነባብሮልህ አይተህ ታውቃለህ ወይ? እግዚአብሄር አንድን ነገር ማድረግ ሲፈልግ ሲፈልግ ባልጠበቅነው መንገድ ሊሰራ እንደሚችል እንዘንጋ።

# ጥናት ሁለት አስቴር 2፡1-23

የጥናት ዓላማ፡- አስቴር ለመቆነጃጀት የፈለገችውን ሁሉ መውሰድ ስትችል ከእግዚአብሄር በሚገኘው ሞገስ ላይ እንዳተኮረች ሁሉ፤ ለእኛም ቢሆን ከእግዚአብሄር ሞገስ የበለጠ ሊያስውበንና ክብር ሊሰጠን የሚችል ምንም ነገር እንደማይኖር ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "...አስቴር ወደ ንጉሡ ዘንድ የምትሄድበት ተራ በደረሰ ጊዜ የሴቶች ልዩ ጥበቃ ቤት ኀላፊ የሆነው ሄጌ የነገራትን እንጂ፣ ሌላ ምንም አልጠየቀችም። አስቴር በሚያዩዋት ሁሉ ዘንድ ሞገስ አገኘች።" አስ 2፡15

1. አስቴር 2፡1-23 በአንድነት ይነበብ። ንጉስ ጠረክሲስ ወደፊት ስለሚኖረው የትዳር ሕይወት ከቅርብ አማካሪዎቹ የተለገሰው ምክር እንደነበረና የተመከረው ምክርም ደስ እንዳሰኘው በቁ1-4 ውስጥ እናነባለን። ይህ ከአማካሪዎቹ የቀረበለት ምክር ምን እንደነበረ አጠር ባለ መልኩ ተናገር።
2. ቁ5-6ትን ስታነብ መርዶክዮስ ስለተባለው ሰው የምታያቸውን መረጃዎች በሙሉ በመዘርዘር ተናገር። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስለ መርዶኪዎስ ከተዘረዘሩት ሃሳቦች መሃል የእስራኤል የመጀመሪያ ንጉስ ከነበረው ከሳዖል ጋራ ይመሳሰላሉ የምትላቸው ነጥቦች የትኞቹ ናቸው?
3. ይህ መጽሐፍ በስሟ የተሰየመላት አስቴር ቁ7ትን ስንመለከት አስቴር ከመባሏ አስቀድሞ መጠሪያ ስሟ ማን ነበረ? የመርዶኪዮስና የአስቴር ግንኙነት ምን እንደነበረና በእነዚህ በሁለት ሰዎች መካከል የነበረው ግንኙነት ምን እንደነበረ ተናገር። ከእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ከአስተዳደጓ ሌላ ስለ አስቴር መረዳት የምንችለው ምን ነገር ይኖራል?
4. በቁ 7 ላይ ስትመለከት አስቴርን የደረሰችበት እንድትደርስ ያደረጋት የእግዚአብሄር ቸርነት ነው ለማለት የሚያስችልህ ምን ነገር ይታይሃል? መለስ ብለህ የራስህን ህይወት ስታየው የእግዚአብሄር ቸርነት ባይሆን ለዚህ አልበቃም ነበር ሊያሰኝህ የሚችል ሁኔታ የሚታይህ ከሆነ ለወገኖች አካፍል።
5. ቁ8-9 የሴቶቹ ጠባቂ ሄጌ በአስቴር ላይ ስለነበረው አመለካከትና ከዚያም የተነሳ ስላደረገላት ነገሮች የሚናገራቸውን ነገሮች ዘርዝር።
6. በአንተ አመለካከት በቁ10 እና በቁ11 ላይ ስለ አስቴር ባህርይ ማየት የምንችለው አንድ ነገር ምንድነው ትላለህ? በቁ12-14 መሰረት ንጉሱ ሚስቱን ለመምረጥ ቢያንስ ቢያንስ ሊፈጅበት የሚችለው ጊዜ ምን ያህል ነው?
7. በቁ 10 ላይ አስቴር ያሳየችው መልካም ባህርይ በቁ20 ላይ ይበልጥ የሚያጎላው ሃሳብ እናነባለን፤ ይህ ሃሳብ ምን እንደሆነ ተናገር? ጠቅላላ ምዕራፍ ሁለትን ስንመለከት ከተለያዩ ሰዎች ዘንድ አስቴር ሞገስ እንዳገኘች ተነግሯል፤ እነዚህ ሁኔታዎች የሚገኙባቸውን ክፍሎች ጠቁም።
8. ወደ ኋላ መለስ ብለን ቁ9ኝን በተለይም ደግሞ ቁ15ትን ስናነብ ምንም እንኳን የፈለገችውን ነገር ጠይቃ መቀበል ብትችልም አስቴር ግን ወደ ንጉሱ በምትገባበት ጊዜ ሄጌ ከነገራት ውጭ ምንም ዓይነት ተጨማሪ ራሷን ማጋጌጫ እንዳልወሰደች፤ በሌላ በኩል ደግሞ በሰዎች ሁሉ ፊት ሞገስ እንዳገኘች እናነባለን። ከዚህ ውስጥ ለህይወታችን መማር የምንችለው እውነት ምንድነው?

# ጥናት ሶስት አስቴር 3፡1-15

የጥናት ዓላማ፡- መርዶኪዮስ አካባቢውን ተመልክቶ አካባቢውን ለመምሰል እንዳልሞከረ ሁሉ፤ እኛ አማኞችም በዙሪያችን ያሉ ሰዎች ሁሉ በሚያደርጉት ነገር ተወስደን የተረዳነውን እውነት በመጣል አካባቢያችንን መምሰል እንደማይኖርብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "…በንጉሡ በር ያሉት የመንግሥቱ ሹማምት ሁሉ ለሐማ ተንበርክከው እጅ በመንሣት አክብሮታቸውን ይገልጡለት ነበር። መርዶክዮስ ግን ወድቆ አልሰገደለትም፤ አክብሮትም አላሳየውም" አስቴር 3፡2

1. አስቴር 3፡1-15 በአንድነት ይነበብ። ቁ1-2 ላይ ያለውን ሃሳብ በመመልከት ሲሆኑ የምታያቸውን ሁኔታዎች በሙሉ አንድ በአንድ በመዘርዘር ተናገር።
2. በቁ2 ላይ የምናነበው ሃስብ ከረጅም ዓመታት በፊት ተመሳሳይ ታሪክ በትንቢተ ዳንኤል ውስጥ ተፈጽሟል፤ ይህ በዚያን ዘመን የተፈጸመው ታሪክ ምን እንደሆነና ከዚህ ጋራ እንዴት እንደሚመሳሰል ለወገኖች ተናገር። በትንቢተ ዳንኤል ውስጥ የሆነው ታሪክ በአብዛኛው አይሁድ ዘንድ የታወቀ ነገር ነው፤ እነዚህ አስደናቂ ወጣቶች ያሳዩት የእምነት ጥንካሬ በመርዶኪዎስ አቋም ላይ ምን ያህል አስተዋጽዖ አድርጓል ብለህ ታምናለህ?
3. በዚህ ክፍል ውስጥ በቁ3-4 ላይ የምናነበውንና በ2፡10-11 ላይ ያለውን ሃሳብ በአንድነት በማንበብ መርዶኪዎስ ለአስቴር ከመከራት ምክር ጋራ እርሱ ለራሱ ሲያደግ ከሚታየው ጋራ በማነጻጸር ስንመለከት በሁለቱ መሃል የሆነ ክፍተት ይታያል፤ ይህ ክፍተት ምን እንደሆነ ተናገር።
4. በቁ3-4 ላይ ስናነብ በንጉሡ በር ያሉት የንጉሡ አገልጋዮች መርዶክዮስን፣ የንጉሡን ትእዛዝ ለምን ትተላለፋለህ? በማለት ጥያቄ ያቀረቡለት ምን ያህል ጊዜ ነበረ? ይህንን ጥያቄ በተደጋጋሚ መጠየቁ ለመርዶኪዮስ የተለየ ሊፈጥርበት የሚችለው ነገር ሊኖር ይችላል ብለህ ታምናለህ ወይ? አስረዳ።
5. መርዶኪዮስ በምዕራፍ 3 ውስጥ ከፍ ከፍ እንዳለው ሁሉ፤ በዘፍጥረት 41 ውስጥ ደግሞ ስንመለከት ዮሴፍ በንጉሱ ዘንድ ከፍ ከፍ መደረጉን ማየት እንችላለን። በአንተ አመለካከት እነዚህ ሁለት ሰዎች በነገሥታቱ ዘንድ ከፍ ከፍ መደረጋቸውን የተጠቀሙበት መንገድ የሚለያየው እንዴት ነው ብለህ ታምናለህ?
6. ቁ5-6ትን በማንበብ፤ ሐማ በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙትን አይሁድ ሁሉ ወደ መግደል ሃሳው ውስጥ ያደረሰው ዋነኛው ነገር ምንድነው?
7. ቁ8-11 ያለውን በሐማና በንጉሱ መሃል የተካሄደውን የሃሳብ ልውውጥ ስንመለከትና እንዲሁም ቁ15 ላይ ለህዝብ ጥፋት አዋጅ አውጀው ከተማይቱ ግራ ተጋብታ እያለች እነርሱ ለመጠጣት መቀመጣቸው ስለ ሐማ ባህርይና ማንነት ምን ይነግረናል? ስለ ንጉሱስ?
8. ቁ2ት ላይ ተመልሰን ስናነብ የመንግሥት ሹማምንቱ ሁሉ ለሐማ እንደሚሰግዱለትና "…መርዶክዮስ ግን ወድቆ አልሰገደለትም፤ አክብሮትም አላሳየውም።" በማለት ይነግረናል። ይህ ሁሉ ሰው የሚሰግድ ከሆነና በተለይም ደግሞ ነገሩ የንጉሥ ትዕዛዝ እንደሆነ ካወቀ ለምንድነው መርዶኪዎስ በእንቢታው ለመጽናት የፈለገው? ለክፋት የሚታዘዙና አምላክ ላልሆነ ነገር የሚሰግዱ ሰዎች መብዛታቸው አንተ ውሳኔህን እንድትቀይር ምን ያህል ግፊት ያደርግብሃል?

# ጥናት አራት አስቴር 4፡1-17

የጥናት ዓላማ፡- መርዶክዮስ ጠንከር ባለ መልኩ እውነትን በመናገር የአስቴርን ሃሳብ እንዳስቀየረ ሁሉ፤ እኛም ለእግዚአብሄር ሥራ መሥዋዕትነት ላለመክፈል ምክንያታቸውን የሚደረድሩትን ሰዎች እውነቱን በግልጽነት በማሳየት ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማገዝ እንደምንችል ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “የአስቴር ቃል ለመርዶክዮስ በተነገረው ጊዜ፣ ይህን መልስ ላከባት፤ አንቺ በንጉሥ ቤት በመሆንሽ ብቻ ሌላው የአይሁድ ሕዝብ ሲጠፋ አንቺ የምትተርፊ እንዳይመስልሽ” አስቴር 4፡12-13

1. አስቴር 4፡1-17 በአንድነት ይነበብ። ቁ1-2 ሲነበብ በሐማ ጠንሳሽነትና በንጉሥ ትዕዛዝ የወጣውን አዋጅ መርዶኪዎስ በምን ሁኔታ ነበረ ያስተናገደው? ለምንድነው መርዶኪዎስ እስከ ንጉሱ በር ብቻ ሄዶ ቤተ መንግሥት ውስጥ ለመግባት ያልቻለው?
2. በቁ3 ላይ ከምናነበው ሃሳብ እንደምንረዳው፤ ይህ ከንጉሥ ዘንድ የወጣው አዲስ አዋጅና ትዕዛዝ በጠረክሲስ ግዛት ውስጥ በሚኖሩ አይሁዶች ምን ያደርጉ ዘንድ ነው ያስገደዳቸው?
3. በቁ4 ውስጥ ከሰፈረው ሃሳብ ስንመለከት ንግሥቲቱ አስቴር የመርዶኪዎስ ሁኔታ ከደንገጡሮቿና ከጃንደረቦቹ በሰማች ጊዜ የወሰደቻቸው እርምጃዎች ምን ምን ነበሩ? አስቴር በዚህ ቁጥር ውስጥ የወሰደቻቸው እርምጃዎች በመርዶኪዎስ ዘንድ ምን ያህል ተቀባይነት ነበራቸው?
4. ቁ5-8 የተላከለት ልብስ የመርዶኪዎስን ችግር የሚፈታ ባለመሆኑ አስቴር ሃታክ የተባለውን ሰው ስትልክ ይታያል። ለአስቴር እንዲያደርስለት ለሃታክ መርዶኪዎስ የሰጠው መረጃዎች ምን ምን ነበሩ?
5. ቁ9-11ላይ መርዶኪዎስ አይሁድን ሁሉ ወክላ ወደ ንጉሱ እንድትገባ ለጠየቃት ጥያቄ አስቴር እንደማይሆንና እንደማይቻል ነገር አድርጋ መልስ እንድትሰጥ ያደረጋት አንድ ነገር ምን ነበረ? አንተስ በህይወትህ ለብዙዎች ደህንነትና መትረፍ ስትል መሥዋዕትነት ለመክፈል ምን ያህል ዝግጁ ነህ?
6. አስቴር መርዶኪዎስ እንድታደርገው ለጠየቃት ነገር የሰጠችው ምላሽ ልክ እንዳልሆነ እንድታውቀውና ይህንን ለማድረግ አለመፈለጓ ለእርሷም ቢሆን መልካም እንዳልሆነ የተናገራትን አራት ሃሳቦች ከቁ12-14 ካለው ክፍል ውስጥ በማውጣት ተናገር።
7. ቁ15-17ትን ስናነብ አስቴር ከላይ ከተናገረችው ምላሽ ወጥታ በተለየ መንፈስ ውስጥ እንደገባች እንመለከታለን። ለመርዶኪዎስ በላከችው በአሁኑ መልዕክቷ ውስጥ የተካተቱት የአስቴር ሃሳቦች ምን ምን እንደሆኑ አስረዳ። እነዚህን ቁጥሮች ስናይ አስቴር አሁን እስከምን ድረስ ለመሄድ ነው የቆረጠችው?
8. ለአይሁድ የሞትና የሽረት ሰዓት በነበረበት ወቅት መርዶኪዎስ በቁ12-13 ላይ እውነት ብሎ ያመነበትን ነገር በግልጽነት ለአስቴር መንገሩ በጊዜው በነበረው አስፈሪ ሁኔታ ውስጥ ያስከተለው ለውጥ ምን ነበረ? አንተስ በሕይወትህ ሰዎች መሥዋዕትነትን ለመክፈል ሲያፈገፍጉ ምን ያህል እውነትን ይዘህ ቻለንጅ ታደርጋቸዋለህ?

# <u>ጥናት አምስት አስቴር 5፡1-14</u>

የጥናት ዓላማ፡- ሐማ ከፊቱ የተዘጋጀለትን ሳያውቅ በትዕቢት ተነፍቶ ከእግዚአብሄር ወጥመድ እንደገባ ሁሉ፤ በእኛም ላይ ሊያጠፋን በክፋት የሚነሳብንን ጠላት ራሱ ባጠመደው ወጥመድ ውስጥ እንዲገባ ማድረግ አምላካችን ዛሬም ቢሆን እንደሚቻለው ለመማር ነው።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ሐማም፣ ምን ይኽ ብቻ አለ፤ ንግሥት አስቴር ባዘጋጀችው ግብዣ ላይ ከንጉሡ ጋር እንድገኝ የጋበዘችው ሰው አንድ እኔ ብቻ ነኝ፤ ነገም ከንጉሡ ጋር ጋብዛኛለች።" አስቴር 5፡12

1. አስቴር 5፡1-14 በአንድነት ይነበብ። በምዕራፍ 4 ውስጥ አስቴር የሚያስገድል እንኳን ቢሆን ወደ ንጉሱ ለመግባት እንደቆረጠች ተመልክተናል፤ በቁ1-2 ላይ አስቴር እንደሰው ስለወሰደቻቸው ጥንቃቄዎች የምታያቸውን ቢያንስ ሁለት ሃሳቦች ተናገር።
2. ቁ1-3 ውስጥ ያለውን ሃሳብ ስናነብ እግዚአብሄር አምላክ ለአስቴር በንጉሱ በጠረክሲስ ዘንድ እጅግ ትልቅ የሆነ ሞገስ እንደሰጣት እናያለን። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ይህንን እውነት የሚያረጋግጡልን ሃሳቦች የትኞቹ ናቸው?
3. ቁ4-9ን ስናነብ ሐማ ከንጉሱ ጋራ ሌላ ማንም ሰው ወደ ንግሥት አስቴር ግብዣ ሳይጋበዝ እርሱ ብቻውን መጋበዙ በውስጡ የፈጠረው ስሜት ምን ነበረ? በእነዚሁ ስድስት ቁጥሮች ውስጥ ስትመለከት በሐማ ውስጥ የተፈጠረውንይህንን ስሜት በዚህ ሰው ውስጥ እንዳይቆይና ቶሎ በአጭሩ እንዲቀጭ ያደረገው ነገር ምን እንደነበረ ተናገር።
4. በቁ10-11 ላይ ሐማ ወዳጆቹንና ሚስቱን ዞሳራን ስብሰባ እንደጠራ እናነባለን፤ የዚህ ስብሰባ ዋነኛ ዓላማው ምንድነው ማለት እንችላለን?
5. ሐማ በቤቱ በጠራው ስብሰባ ላይ ለተገኙት ሰዎች ከነገራቸው ዋና ዋና ነጥቦች መሃል ጸሐፊው ያሰፈረልን ሃሳቦች ምን ምን ነበሩ?
6. በአስቴር 3፡10 ላይ የአይሁድ ጠላት በማለት የሚጠራው ሐማ በንጉሥ ጠረክሲስ ዘንድ ታላቅ ሞገስ በማግኘቱና ከመኳንንቱ ሁሉ በላይ ከፍ በማለቱ ያገኘውን ደስታ የቀማው ነገር እንዳለ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እናነባለን፤ ይህ ለደስታው እንቅፋት የሆነው ነገር ምን እንደሆነና የት ሥፍራ እንደሚገኝ ተናገር።
7. በቁ14 ላይ ስንመለከት ሐማ ደስታውን ከሚሰርቅበት ነገር መገላገል የሚችልበትን ምክር ያገኛል። በዚህ ቁጥር ውስጥ መፍትሔ ሆኖ የተሰጠው ምክር ምን ነበረ?
8. በቁ12 መሰረት የንግሥት አስቴር እርሱን ብቻ ከንጉሱ ጋር ወደ ግብዣዋ መጥራቱም በምን መንገድ ነበረ ሃማ የተመለከተው? ከዚህ የእግዚአብሄር አሰራር ምን መማር እንችላለን? እግዚአብሄር የማይለወጥ አምላክ ስለሆነ በዚያን ጊዜ አይሁድን ለመታደግ ሲያደርገው የምናየውን ነገር ዛሬም በአንተ ወይም በአንቺ ሕይወት ውስጥ ሊደግመው እንደሚችል መጠራጠር አያስፈልግም።

# ጥናት ስድስት አስቴር 6፡1-14

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር ከእርሱ ጋራ የቆመን ሕዝብ ሊቋቋምና ድል ሊያደርግ የሚችል ምንም ዓይነት ሃይል እንደሌለ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ዘሩ ከአይሁድ ወገን ከሆነ፣ ልትቋቋመው አትችልም፤ ያለ ጥርጥር ትጠፋለህ አሉት።” አስቴር 6፡13

1. አስቴር 6፡1-14 በአንድነት ይነበብ። በቁ1 ላይ ጸሐፊው “በዚያች ሌሊት” በማለት የሚናገርላት ስለየትኛይቱ ሌሊት እንደሆነ ተናገር። በዳን 2፡1 እና 6፡18 ላይ ንጉስ ናቡከደነጾርና ንጉስ ዳርዮስን እንቅልፍ ከነሳቸው ነገር የዚህን ሰው እንቅልፍ ማጣት ልዩ የሚያደርገውን ነገር ምንድነው?
2. አስቴር 6፡1-2 ትን በማንበብ ይህ ታሪክ በአጋጣሚ ሳይሆን የእግዚአብሄር እጅና እርሱ ያቀነባበረው ነገር እንደሆነ ሊጠቁሙ ይችላሉ የምትላቸውን ሃሳቦች ሁሉ በመዘርዘር ተናገር።
3. በቁጥር 1-3 በምናያቸው ክፍሎች መርዶኪዎስ ይህንን የመሰለ በጎነት ለንጉሥ ጠረክሲስ አድርጎ ያለ ምንም ዓይነት እውቅና ቆይቶ ዛሬ በንጉሱ መታሰቡ ለእኛ ሕይወት ምን ያስተምረናል?
4. ቁ4 ላይ ንጉሱ የጠየቀው ጥያቄና በዚያው ሰዓት ደግሞ የሐማ በዚያ መገኘት እድላዊ የሁኔታዎች መገጣጠም ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? አይደለም የምትል ከሆነ ምን ሊሆን እንደሚችል ውይይት ይደረግበት።
5. በቁ6 ላይ ንግሥ ለጠየቀው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ሐማ ለራሱ ያቀረበው ጥያቄ ምን የሚል ነበረ? ለራሱ በማሰብ ከቁጥር 7-9 የምናነበውን ሁሉ እናውቃለን፤ የሚደረግለት መርዶክዮስ እንደሆነ አስቀድሞ አውቆ ቢሆን ኖሮ የሚሰነዝረው ሃሳብ የተለየ ይሆን ነበረ ወይ? ተወያዩበት።
6. በቁ12 ላይ ሐማ አዝኖና ራሱን ተከናንቦ ወደ ቤቱ እንደሄደ እናነባለን። ይህንን ሃሳብ በመዝ 23፡5 ላይ “በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ” ከሚለው ሃሳብ ጋራ እንዴት ታዛምደዋለህ?
7. በቁ13 ላይ “ዘሩ ከአይሁድ ወገን ከሆነ ልትቋቋመው አትችልም” በማለት በአህዛብ አንደበት መነገሩ፤ ለእግዚአብሄር ህዝቦች በውስጣቸው ሊፈጥር የሚገባው ነገር ምንድነው?

# ጥናት ሰባት አስቴር 7፡1-10

የጥናት ዓላማ፡- የእግዚአብሄር ሞገስ በላያችን ላይ ሲኖር ሰዎች በራሳቸው ተነሳሽነት ጉዳያችንን እንዲፈጽሙልን ማድረግ የሚችል አምላክ እንዳለን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ስለዚህ ንጉሡና ሐማ ከንግሥት አስቴር ጋር ለመጋበዝ ሄዱ፤ በሁለተኛውም ቀን የወይን ጠጅ እየጠጡ ሳለ፣ ንጉሡ እንደ ገና፣ ንግሥት አስቴር ሆይ፤ የምትለምኚው ምንድን ነው? ይሰጥሻል" አስ 7፡1-2

1. አስቴር 7፡1-10 በአንድነት ይነበብ። በቁ 3 ላይ ብቻ በመመርኮዝ አስቴር ንጉሱን የጠየቀቻቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው?"
2. በቁ 3 ላይ "ሕይወቴን ታደጋት" ብላ ያቀረበችው ጥያቄ፤ እንደምናውቀው አስቴር ንግሥት እንዲሁም ዘሯ እንኳን አይሁዳዊ እንደሆነ ያልተናገረች ሆኖ እያለ በምን ምክንያት ነው የዚህ ዓይነት ልመና የምታቀርበው?
3. ንግሥት አስቴር የአይሁድን ህዝብ እንደ ራሷ ህዝብ እና የአይህዳውያኑንም ህይወት እንደ ራሷ ህይወት አድርጋ ለንጉሥ ጥያቄ ማቅረቧ፤ ዛሬ በዚህ ዘመን ላለነው አማኞች ሊያስተምረን ይችላል?
4. በአስ 4፡12-14 ላይ መርዶኪዎስ ለንግሥት አሥቴር ጠንከር ባሉ ቃላት ያስተላለፈው መልዕክት፤ በዚህ ክፍል በቁ 3-4 ላይ አስቴር ለንጉስ ጠረክሲስ ለምትናገረው ነገር ምን ያህል አስተዋጽዖ አድርጓል ብለህ ታምናለህ?
5. መርዶኪዎስ አስቴር በ4፡9-11 ላይ ለመጀመሪያ ጥያቄው የሰጠችውን ራስ ወዳድ መላሽ ሳይቀበል ሁለተኛውን መልዕክት የማስተላለፉ፤ በአየቃላይ ሁኔታው ላይ ያስከተለውን ውጤት እንዴት ታየዋለህ?
6. በቁ 5-7 ውስጥ ከምናነበው ያ ክፉ ሃማ በብዙ ፍለጋና ጥረት፣ ብዙ ውድድርን አልፋ በተገኝች በሚስቱ በአስቴር ህይወት ላይ እንደመጣበት ባወቀ ጊዜ ንጉስ ጠረክሲስ የተሰማው ስሜት ምን እንደሚመስል አስረዳ። ጠረክሲስን የአስቴር ነገር ይህን ያህል ካስቆጣው፤ በሞቱ ያፈራትን ሙሽራውን ቤተ ክርስትያን ጠላት ሰይጣን ለማጥፋት ሲነሳ ኢየሱስ ምን ያህል ሊያስቆጣው እንደሚችል በማነጻጸር ተወያዩበት።
7. በጥቂት ምዕራፎች ውስጥ ሐማ የንጉሥ ቀኝ እጅ ብቻ ሳይሆን የፈለገውን ማስፈጸም የሚችል ሰው ሆኖ እያለ በጥቂት ቀናት ውስጥ ለስቅላት መብቃቱ ስለ እግዚአብሄር አሰራ ምን የሚነግረን ነገር አለ?
8. ወደ ኋላ መለስ ብለን ቁ1-2 ላይ ስናነብ በተለይም በቁ2 ላይ ንግስት አስቴር ከራሷ ምንም ነገር ሳታሰማ ንጉሱ ራሱ ፍላጎቷን ለማሟላት ዝግጁ እንደሆነና የምትፈልገውን እንድትጠይቀው ሲጠይቃት በምዕራፍ 5 ውስጥ ከጠየቃት ሌላ እንደገና ይጠይቃታል። ከንጉሱ በራሱ ተነሳሺነት ለማድረግ መነሳሳቱ ስለ እግዚአብሄር ሞገስ የሚያስተምረን እውነት ምንድነው?

# ጥናት ስምንት አስቴር 8፡1-17

የጥናት ዓላማ፡- ከሰው አንዳች ነገር ሳንጠብቅ ተገቢውን ቸርነት ስናደርግ፤ እግዚአብሄር ቀን ቆጥሮ በረከቱን ሊያፈስብን እንደሚችል ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ንጉሡ ከሐማ መልሶ የወሰደውን ባለ ማኅተም ቀለበት አውልቆ ለመርዶክዮስ ሰጠው፤ አስቴርም መርዶክዮስን በሐማ ቤት ንብረት ላይ ሾመችው።" አስቴር 8፡2

1. አስቴር 8፡1-17 በአንድነት ይነበብ። በቁ1 ላይ ስንመለከት፤ የሐማ ንብረት ሁሉ ለአስቴር መሰጠቱን ሲናገር "በዚያኑ ዕለት" ይላል። ይህ አባባል ስለ እግዚአብሄር ፍርድ የሚነግረን ነገር ምንድነው?
2. በአስ 4፡16 ላይ "...ነገሩ ምንም እንኳ ከሕግ ውጭ ቢሆንም፣ ወደ ንጉሡ ዘንድ እሄዳለሁ፤ ከጠፋሁም ልጥፋ።" ብላ በወሰነችው ውሳኔና፤ በ8፡1 ላይ በሚታየው ያልተጠበቀ ውጤት መሃል ያለውን ነገር አስረዳ። በአስቴር ላይ የሆነው ይህ ታሪክ ለእያንዳንዳችን ህይወት ምን ልንማርበት እንችላለን?
3. የንግሥት አስቴር ከመርዶኪዎስ ጋራ ስላላቸው ግንኙነት አስመልክቶ በአስ 2፡10 እና በአስ 8፡1 የሰፈሩትን ሃሳቦች በማንበብ ተቃራኒ የሚመስሉትን ሃሳቦች እንዴት ማስታረቅ እንደሚቻል አስረዳ።
4. በቁ3-4 ላይ ስንመለከት አስቴር ሌላ ተጨማሪ ልመና ለንጉሱ ታቀርባለች፤ ይህንን ለማድረግ ድፍረት የማግኘቷ ምክንያት ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
5. ቁ5ትን እና ቁ6ትን ስናነብ፤ ንግሥት አስቴር ይህንን ጥያቄ ለንጉስ ለማቅረብ ያስገደዷትን ምክንያቶች ምን በማለት ነው ያቀረበችው? እኛስ እንደ እግዚአብሄር ህዝብና እንደ እግዚአብሄር ቤተሰዎች ከንግሥት አስቴር ልንማር የምንችለው ነገር ምን እንደሆነ ተናገር።
6. ቁ7-12 በማንበብ በተለይም ቁ8 "መልካም መስሎ የታያችሁን ሌላ ዐዋጅ በንጉሡ ስም ጽፋችሁ በንጉሡ የቀለበት ማኅተም ዐትሙት" የሚለውን ስታነብ ንጉሱ ለአስቴርና ለመርዶኪዎስ ስለሰጠው ስልጣን ምን ታያለህ? እነዚህን ቁጥሮች ስታይ እንደ እግዚአብሄር ሰዎች አግባብ ባለው መንገድ ተፈጻሚ አድርገውታል ብለህ ታምናለህ ወይ?
7. መርዶኪዎስና አስቴር የተጓዙበት አስፈሪና ወሳኝ የሆነው የእምነት ጉዞ ውጤቱ በቁ15-17 ሰፍሯል። ከውጤቶቹ ውስጥ ለአንተ ግልጽ ሆነው የሚታዩህን ቢያንስ ሶስት ነገሮች ተናገር።
8. ቁ2 "አስቴርም መርዶክዮስን በሐማ ቤት ንብረት ላይ ሾመችው" ይላል። መርዶኪዎስ የሙት ልጅ የሆነቸውን አስቴርን ለማሳደግ ሲወስን ከእርሷ የጠበቀው ነገር ነበረ ወይ? ለሰዎች ስለምታደርገው ቸርነትና የእግዚአብሄርን በረከት አስመልክቶ ከዚህ ክፍል ምን ትማራለህ?

# ጥናት ዘጠኝ አስቴር 9፡1-10፡3

የጥናት ዓላማ፡- በሕይወቱ ቆርጦ ለሃማ አልሰግድም ያለውን መርዶክዮስን ለክብር ያበቃ እግዚአብሄር፤ ዛሬም በስሙ ተማምነው በእምነት ጸንተው የሚቆሙትን ልጆቹን በጠላቶቻቸው ፊት ከፍ ከፍ እንደሚያደርግ ለመማር። የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "…ይህን ያደረጉትም መርዶክዮስን ስለ ፈሩ ነበር። መርዶክዮስ በቤተ መንግሥቱ ታዋቂ ሆነ፤ ዝናው በየአውራጃው ሁሉ ተሰማ፤ ኀይሉም እየበረታ ሄደ።" አስቴር 9፡3-4

1. አስቴር 9፡1-10፡3 በአንድነት ይነበብ። ቁ1ድን ስንመለከት የአይሁድ ጠላቶች ድል የእነርሱ እንደሚሆን እርግጠኞች ነበሩ፤ ታዲያ አይሁድ በጠላቶቻቸው ላይ የበላይነትን እንዲቀዳጁ የሆነበት ዋነኛ ምክንያት ምንድነው ትላለህ? ለእኛ ለክርስትያኖች ከዚህ ሃሳብ ጋራ ማነጻጸር የምንችለው እውነት ካለ አስረዳ።
2. ቁ3 እና 4ትን በማንበብ መርዶኪዎስን አስመልክቶ ከየተነገሩት ነገሮች ቢያንስ ሶስቱን ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። በዚህ ሁኔታ መሃል መኳንንቶቹ፣ እንደራሴዎቹና፣ ገዢዎቹ ሁሉ የአይሁድን ሕዝብ ለመርዳት የመነሳታቸው ምክንያት ምን ነበረ?
3. ቁ10፣ ቁ15ትና፣ ቁ16 ላይ "በምርኮው ላይ ግን እጃቸውን አልዘረጉም" የሚል ሃሳብ ሰፍሯል። በዚህ አነጋገሩ ላይ ጸሐፊው ምን ለማለት የፈለገ ይመስልሃል? የአይሁድ ህዝብ በከተማው ያለውን ሁሉ ጠራርገው ማጥፋት ሲችሉ፤ ይህንን አለማድረጋቸው ምን ያሳየናል?
4. ቁ18-21 ላይ ህዝቡ ሁሉ ዕለቱንም የተድላና የደስታ ቀን አድርገው እንደ ዋሉ የሚናገር ከሆነ፤ ታዲያ መርዶኪዎስ ለአይሁድ ሕዝብ በሙሉ ደብዳቤ መጻፍና መላክ ለምን አስፈለገው? የመርዶኪዎስን የደብዳቤ ይዘት ስትመለከት ለህይወትህ ምን ትምህርት ሊሆንህ እንደሚችል ለወገኖች ተናገር።
5. በዚህ በምዕራፍ 9ኝ ውስጥ ንጉሱን ከቁ14 በኋላ አናየውም። ከዚህ ቁጥር በኋላ በተለይም ከቁ29-32 ውስጥ ማንም የበላይ ያለባቸው በማይመስል መንገድ ነገሮችን ማካሄዳቸው ከንጉሱ ጋራ ስላላቸው ግንኙነት ምን ያሳየናል?
6. አስቴር 10፡1-3ትን በማንበብ መርዶኪዎስ ስለተባለው ሰው የምታየውን ሁሉ በመዘርዘር ተናገር። ስለዚህ ሰው ከዘረዘርካቸው ነገሮች በሙሉ የምታደንቀው ነገር ምንድነው?
7. መለስ ብለን ቁ3-4ትን በማንበብ፤ መርዶኪዎስ ዛሬ በዚህ ክፍል ውስጥ ወደምናነበው የከፍታ ህይወት ላይ ለመድረስ ያለፈባቸውን ሁኔታዎች ከቀደሙት ምዕራፎች በመነሳት በአጭሩ ተናገር። ከመርዶኪዎስ ሕይወት ለራስህ ምን ተምረህ ለመለወጥ ትወዳለህ?